ባህረ ጥበባት

ፍቁረ እግዚእ ሰ/ት/ቤት

ቤተ ክርስቲያን ባህረ ጥበባት

34ኛ ዕትም ቅፅ 5 ቁጥር 10 ነሐሴ 2014 ዓ.ም



“ በአውሎ ነፋስና በመብረቅ ንውጽውጽታ
ከጌቴሴማኔ ከመቃበሩ ቦታ ወደ ላይ ወደ ሰማይ ዐረገች “
ነግሥ ዘፍልሰታ



በደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ እና መካነ ጎልጎታ
ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን
የፍቁረ እግዚእ ሰንበት ትምህርት ቤት
ትምህርት ክፍል
በትምህርታዊ ጽሑፍ ዝግጅት ክፍል ተዘጋጀ

ማውጫ

3 ፩. በረከተ ወንጌል
“ጸምን ቀድሱ “ ኢዩ 1፣ 14

6 ፪. ምን እንጠይቅሎ?
ቤተክርስቲያን ለምንድነው በቅዱሳን ስም የምትሰየመው?

8 ፫. ዝክረ ቅዱሳን
አቡነ ዓቢየ እግዚእ

11 ፬. ሰሞንኛ
ደብረ ታቦር

12 ፭. ነገረ ሃይማኖት
‹‹ እመ እግዚአብሔር - የእግዚአብሔር እናት››

14 ፮ . ብሂለ አበው
በእንተ ጸም

15 ፯. ኪነ ጥበብ

17 ፰. ወቅታዊ
ፍልሰታ ለማርያም

20 ፱. ከሰሞኑ በረከት
ጽንሰታ ለማርያም



፩.በረከተ ወንጌል

“ጾምን ቀድሱ “ ኢዩ 1፣ 14

ክርስቲያኖች ሁላችን ፍቃደ ሥጋችንን ለፍቃደ ነፍሳችን ማስገዛት እንችል ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ መንፈሳዊ በረከት እንቀበል ዘንድ የሰይጣንን ፈተና ድል እናደርግ ዘንድ አብዝተን ልንፈጽማቸው ከሚገቡ መንፈሳዊ ተግባራት መካከል አንዱ ጾም ነው ። ከቤተ ክርስቲያ የሥርዓት መጻሕፍት መካከል አንዱ የሆነው ፍትሐ ነገስት የጾምን ትርጉም ሲያስቀምጥ ጾም ማለት ለታወቀ ሰአት ከምግበ ሥጋ መከልከል ማለት ነው ይላል ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ ›› መዝ 108፡-24 እንዳለ ከጥሉላት ምግብ ርቆ ‹‹ ክብርት በምትሆን በአርባ ጾም መጀመሪያ ሱባኤ 12 ሰዓት ከቅድስት ሰኞ ጀምሮ እስከ ኒቆዲሞስ አርብ 11 ሰዓት ሰሙነ ሕማማትን 13 ሰዓት ጹሙ ›› እንዲል ፍትሐ ነገስት ለታወቀ ጊዜ ከየትኛው ምግብ ራስን መከልከል ጾም ይባለል።

ጾም ማለት ከምግብ መከልከል ማለት ቢሆንም ከምግብ መከልከል ሁሉ ግን ጾም አይደለም ሰው በተለያየ ምክንያት ራሱን ከምግብ ሊከለክል ይችላልና አንዳንዱ በሕመም አንዳንዱ በማጣት የተነሳ ከምግብ ሊከለከል ይችላልና አንደ አይሁድ ያለው ለክፋት ስራው ከምግብ መከልከልን እንደ መማማያ ሊያደርገው ይችላል ‹‹ጳውሎስን ይዘን እስክንገድለው ምንም እንዳንቀምስ ተማምለናል አሉ ›› ሐዋ 23፣14 ከምግብ መታቀባችን ጾም የሚሆነው ስለጽድቅ ካደረግነው ነው ጌታችን ስለጽድቅ የሚራቡ እና የሚጠሙ ብጹአን ናቸው እንዳለ።

አምላካችን እግዚአብሔር በነቢዩ በኢዩኤል ላይ አድሮ የእግዚአብሔር በረከት ከእስራኤል ጠፍቶ በምትኩ መቅሠፍትና መዓት ረሃብና ቸነፈር በመጣባቸው ጊዜ (ኢዩ 1፡1-13) ‹‹ እናንተ የአምላኬ አገልጋዮች፥ ኑ፥ ሌሊቱን ሁሉ በማቅ ላይ ተኙ። ጾምን ቀድሱ፥ ጉባኤውንም አውጁ ሽምግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፥ ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ ›› አላቸው በዚህ ቃል ውስጥ በጾም የሚገኝ መንፈሳዊ በረከትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ልናገኝ የምንችለው ጾማችንን በመቀደስ እንደሆነ ነቢዩ ይነግረናል ። ጾምን እንዴት መቀደስ ይቻላል

ከስብከቱ ጣዕም የተነሣ አፈ ወርቅ የተሰኘው ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ጾምን በሁለት ዐበይት ነገሮች መቀደስ እንደሚገባ ያስተምራል አንደኛው የምንጾምበትን ምክንያት በመቀደስሲሆን ሁለተኛው የምንጾምበትም መንገድ በመቀደስ ነው ።

ለምን እንጾማለን

የክርስቲያች ጾም ዋነኛ ዓላማ ሊሆን የሚገባው ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የተነሣ በተሰበረ ልብ ከእርሱ ጋር እንድንጣበቅ ሊሆን ይገባል በዚህ ወቅት ሥጋዊ ብልቶቻችን በነፍሳችን መንገድ ላይ እንቅፋት እንዳይሆኑ ይልቁንም በጾም አማካኝነት ከነፍሳችን ጋር ተባብረው እንዲሰሩ ማስማማት ይገባል በዚህ ዓይነት መልኩ በምንጾምበት ጊዜ በነፍሳችን ውስጥ እንድንኖር ከቁሳዊና ከሥጋዊ ደረጃ በላይ ከፍ እንላለን ይህንንም የምናደርገው መንፈሳችንንና ነፍሳችንን በአሰራሩ ውስጥ ካለው

ካለው ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር አንድ ለማድረግና በእግዚአብሔር ፍቅርና ወዳጅነት ለመደሰት ነው።ሌላው የጾም ዓላማችን ሊሆን የሚገባው እግዚአብሔርን ወደ እኛ ለማቅረብ ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስን ከእኛ ለማራቅ ሊሆን ይገባል ‹‹እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል›› (ያዕ 4፡8) ተብሎ እንደተፃፈልን።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የምንጾመው በሁለት ዐበይት ምክንያቶች ነው ይላል አንደኛው፥ ራሳችንን ከዚህ ዓለም ነገሮች ከእነርሱ ዋናውም ከምግብ አርቀን ወደ መንፈሳዊ ነገሮች እንድናቀርብ ስለሚፈልግ ነው። በየጊዜው በየሰዓቱ ስንበላ ሥጋችን ተድላ ደስታ ያደርጋልና። በመሠረቱ ምግብ በልቶ ደስ መሰኘት በራሱ ነውር ኾኖ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር የአማናዊ ተድላና ደስታ ምንጩ መንፈሳዊ ተግባር እንደኾነ እናስብ ዘንድ ይሻል። ስለዚህ እንድንጾም የሚፈልገውና በዚያውም ውስጥ እንድናስተውለው የሚፈልገው የመጀመሪያው ምክንያት ይኸው ነው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ማጣት ዘወትር እንዲራቡ ከሚያደርጋቸው ሰዎች ጋር አንድነትና ኅብረት እንዲኖረን ስለሚሻ ነው። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተከትለን በየጊዜው ልንጾም እንችላለን። ይህ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አስገድዶአቸው ሳይኾን እጦት አስገድዶአቸው ያለማቋረጥ ዘወትር የሚጾሙ ሰዎች ግን አሉ። እግዚአብሔር ደግሞ ለእነዚህ ሰዎች እውነተኛ ፍቅር እንድናሳይ ይፈልጋል። አጥቶ የመራብ ትርጕሙ ምን ማለት እንደኾነ እኛው ራሳችን በተግባር እንድናይ ይሻል። በጾማችን ውስጥ እንድናፈራው የሚፈልገው አንዱ ፍሬ ይኼ ነው። ጾም የፍቅረ ቢጽ እናት ነች የምንለውም ለዚህ ነው።

እንዴት እንጹም

የነነዌ ሰዎች ጾመዋል፤ የእግዚአብሔር ምሕረትንም አግኝተዋል (ዮና.3፡10)። እስራኤላውያንም ጾመው ነበር፤ ነገር ግን እያጉረመረሙ ተመለሱ እንጂ በመጾማቸው አንዳች ጠቀሜታን አላገኙም (ኢሳ.58፡3-7፣ 1ኛ ቆሮ.9፡26)። ስለዚህ እንዴት መጾም እንዳለባቸው ለማያውቁ ሰዎች የጾም ጉዳቱ ትልቅ ነውና በጥርጣሬ እንዳንኼድ፣ እንዲሁ አየርን እንዳንደልቅ፣ እንዲሁ ከጨለማ ጋር እንዳንጋደል፥ ይህን የምናከናውንባቸውን ሕጎች ልንማር ያስፈልገናል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዐቢይ ጾም እኩሌታ በሰጠው ትምህርት ጾም መድኃኒት ናት። አወሳሰድዋን በትክክል ላላወቁ ግን ጥቅም የላትም። ይህችን መድኃኒት የሚወስድ ሰው በየስንት ሰዓቱና በምን ያህል መጠን እንደምትወሰድ፣ ለምን ዓይነት በሽታ እንደምትጠቅም፣ በየትኛው አከባቢና የአየር ኹናቴ እንደምትወሰድ፣ ከእርሷ ጋር የሚኼዱና የማይኼዱ ምግቦችን እንዲሁም ከእርሷ ጋር የማይስማሙ ሌሎች ነገሮችን ለይቶ ማወቅ አለበት። እነዚህን ግምት ውስጥ አስገብቶ የማይወስዳት ሰው ግን ከጥቅሟ ይልቅ ጉዳቷ ታመዝንበታለች። አንድ በሐኪም የታዘዘልንን የደዌ ዘሥጋ መድኃኒት እንዲያሽለን ስንፈልግ በጥንቃቄ ልንወስደው ያስፈልጋል፤ የነፍሳችንን ደዌና በአእምሮአችን ውስጥ ያሉ ቁስሎችን ለመፈወስ ብለን በምንወስደው መድኃኒት ደግሞ ከዚህ የበለጠ መጠንቀቅ ይገባናል ይላል።

ስለዚህ ስንጾም

1. በእውነተኛ መታቀብ ሊሆን ይገባል ቅዱስ ያሬድ ይጹም ዓይን ይጹም ጆሮ ይጹም አፍ እንዳለ እውነተኛ ጾም የስሜት ሕዋሳትን ወደ ኃጢአት ከሚወስድ መንገድ እና ከኃጢአት መጠበቅ ነው ።ዜና አበው የተሰኘው ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ጾምን ልጓመ ሥጋ ያላት ከዚህ የተነሣ ነው ፡ ፡ ቅድስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጾም ሁለንተናን ከኃጢአት ማቀብ ነው ይላል ቢያንስ በጾማችን ወቅት ልማድ ከሆኑብን ኃጢአቶች ማለትም ክፉ ከመናገር ፣ማንንም ሰው እንደ ጠላት ከማየት. እና ልምድ ካደረጋችሁት መሐላ እራቁ ሲል ይገስጻል ።
2. ከሌሎች ምግባር ትሩፋቶች ጋር አብሮ ማድርግ ከሦስቱ የመጽሐፈ መነኮሳት መካከል አንዱ የሆነው ማር ይስሐቅ ላይ ጾምን የምግባሮች ሁሉ እናት ይላታል ጾም የበጎ ነገር ሁሉ መቅድም ናት።

‹‹ ጾም ሙሽሪትን ትመስላለች፤ ሙሽሪትን በሠርግ አዳራሽ ኾነው የሚቀበሏት ሰዎች ቤቱን ያስጌጡታል፤ ይሸልሙታል። ወደ ሠርጉ አዳራሽ የሚገባውን ሰው የሠርግ ልብስ ለብሶ እንደኾነ፣ የቆሸሸ እንዳልኾነ አይተው ያስገቡታል። እኛም እንዲኽ ልንኾን ይገባናል ብዬ እነግራችኋለኹ። ልቡናችንን በማንጻት፣ ልል ዘሊል ከመኾን በመራቅ፣ የክፋት እርሾን በማስወገድ፣ ከጾም ጋር አብረው የሚመጡትን የሚያጅቧትን መልካም ምግባራትንም ለመቀበል የልቡናችንን ውሳጤ በመክፈት የምግባር እናት፣ የማስተዋል እንዲኹሉም ለሌሎች ምግባራት ኹሉ ንግሥት የምትኾን ጾምን ልንቀበላት ይገባናል ብዬ እነግራችኋለኹ። ይኽን ያደረግን እንደኾነ ታላቅ ሐሴት እናደርጋለን፤ ርሷም ቁስለ ነፍሳችንን ትፈውስልናለች›› ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ጾም ቍስለ ነፍስን የምትፈውስ፣ ኃይለ ፍትወትን የምታደክም፣ የበጎ ምግባራት ኹሉ መጀመሪያ፣ ጸጋ እግዚአብሔርን የምታሰጥ፣ ለጽሙዳን ክብራቸው፣ ለደናግል የንጽሕና ጌጣቸው፣ የጸሎት እናት፣ የዕንባ መገኛ ምንጭ፣ አርምሞን የምታስተምር፣ ለበጎ ሥራ ኹሉ የምታነቃቃ፣ ሰውነትን በእግዚአብሔር ፊት በማዋረድ ትሕትናን ገንዘብ ለማድረግ የምትረዳ መድኃኒተ ነፍስ ናት›› እንዲል ማር ይስሐቅ አንቀጽ 4 በጾም ወቅት መጸለይ፣ መመጽወት፣ መስገድ በጾም የምናገኘውን ዋጋ ከፍ ያደርገዋል።

ጾማችንን ቀድሰን በረከትን እናገኝ ዘንድ የአምላካችን ቅዱስ ፍቃድ ይሁንልን ።

፪. ምን እንጠይቅሎት

ቤተክርስቲያን ለምንድነው በቅዱሳን ስም የምትሰየመው?

ቤተክርስቲያን "ቤት" እና "ክርስያን" ከሚሉ ሁለት የግዕዝ ቃላት የመጣ ቃል ነው። ቤት ቤተ ካለው ግስ ሲመዘዝ ትርጉሙም አደረ ማለት ይሆናል። ስለዚህ ቤት ማደርያ መኖርያ ማለት ነው። ክርስቲያን ደግሞ ክርስቶስን የሚከተል፣ ክርስቶሳዊ፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኖ የተጠመቀ ማለት ነው። ክርስቶስን የሚከተል ሲልም ሕጉን (አታድርግ የሚለውን) የሚያከብር፤ ትዕዛዛቱን (አድርግ የሚለውን) የሚፈጽም ማለት ነው። አንድ ላይ አገናኝተን ስንተረጉመው ቤተክርስቲያን ማለት የክርስትያኖች መኖርያ፣ መሰብሰቢያ፣ መማማርያ፣ መጸለያ ቅዱስ (የተመረጠ) ቦታ ማለት ነው። የእንግሊዘኛው Church የሚለው ቃል ኪርያኮን (kyriakon) ከሚለው የግርክ ቃል የመጣ ነው። ኪሮስ(kyrios) ማለት ጌታ ማለት ሲሆን ኪርያኮስ (kyriakos) ሲሆን ደግሞ የጌታ ማለት ይሆናል። በአጠቃላይ ኪርያኮን ማለት የጌታ ቤት/አካል ማለት ነው። ከቤተክርስቲያን ጋር የተገናኘው ሌላኛው ቃል ecclesiastical የሚለው ነው። ይህም አቅሌስያ (ekklēsiastēs) ከሚለው የግርክ ቃል የወጣ ሲሆን የተመረጡ/ የተጠሩ ሰዎች ሕብረት ማለት ነው። አንድም በ254 ዓ.ዓ ብሉይ ኪዳንን በበጥሊሞስ ሦስተኛ ትእዛዝ ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ/ግሪክ የተረገሙት ሰባው ሊቃውንት ከሐል የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል አቅሌስያ በሚል ተርጉመውታል። ትርጉሙ ጎሩያነ እግዚአብሔር/ የእግዚአብሔር ምርጦች ወይም እግዚአብሔር የመረጣቸው ማለት ነው። የቃላቱን መነሻ እንድናይ ያስፈለገበት ምክንያት የቃላቱ ምንጫቸው ቤተክርስቲያናችን ቃሉን በዘይቤያዊ ፍቺ ከምትፈታበት መንገድ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ስለሆነ ነው።

ቤተክርስቲያን በዘይቤያዊ ፍቺ **በሦስት መንገድ ይፈታል።** የመጀመርያው እያንዳንዱ ክርስቲያን ቤተክርስቲያን ነው የሚለው ነው። ሁለተኛው የክርስትያኖች ሕብረት ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ ሕንጻ ቤተክርስቲያኑ ነው። በተለይ የመጀመርያው በኋላ የተነሳንበትን ጥያቄ ለመመለስ ስለሚረዳን በጥልቀት ሊታይ ይገባል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ስንል ምን ማለታችን ነው? ዝም ብሎ ለይስሙላ ማተብ ያንጠለጠለውን በሙሉ ነው? ወይስ ክርስቲያን ለመባል መስፈርት አለው? ክርስቲያኖች በግለሰብ ደረጃ ቤተክርስቲያን የተባሉት ከላይ ባነሳነው የቃሉ ብያኔ የተነሳ ነው። ቤተክርስቲያን ማለት የጌታ ቤት/ማደርያ ማለት ነው ብለናልና በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሰውነት ውስጥ እግዚአብሔር ያድራል። ቅዱስ ጳውሎስ እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ናችሁ ሲል ይህንንኑ ማለቱ ነው። 1ቆሮ 3÷16 እግዚአብሔር በሰውነታችን እንዲያድር ግን ቅድመ ሁኔታዎች አሉት። ጌታችን ስለነዚህ መስፈርቶች ደጋግሞ በዮሐንስ ወንጌል ላይ ይናገራል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14÷23 ላይ ጌታችን "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል። አባቴ ይወደዋል፤ ወደእርሱም እንመጣለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖርያ እናደርጋለን" ይላል። ይህን የትዕዛዝ ጉዳይ ሲያብራራ ደግሞ በዮሐ 6÷56 ላይ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራልና፤ እኔም በርሱ እኖራለሁ።" ይላል። ይህ የሱታፌ አምላክ (Synergy) ሃሳብ የሃይማኖታችን መሰረት ነው። ክርስትና ሲባል በአጭሩ በእኛ ውስጥ ክርስቶስ እንዲኖር የማድረግ ተግባር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስቀመጠው ደግሞ የጌታ አካል መሆን።

(ከላይ ኪርያኮን የሚለውን ቃል ትርጉም ልብ ይሏል።) ነጻ ፈቃድን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ነው። በእኛ ውስጥ እግዚአብሔር እንዲሰራ ማድረግ። ለእግዚአብሔር እጅ ሆኖ የወደቁትን ማንሳት፤ ለእግዚአብሔር እጅ ሆኖ የተራቡትን ማብላት፣ የታረዙትን ማልበስ ወዘተ... ከሁሉ በላይ ደግሞ ሰዎችን ወደ ድኅነት መጥራት። ይህ እንዲሆን የፍቃድ ስምምነት ያስፈልጋል። ራስ እጅ እንዲሰራ ትዕዛዝ ሲልክ እጅ አሻፈረኝ ማለት አይችልም። ትዕዛዙን መቀበል አለበት። በቤተክርስቲያን ውስጥም ራስ የተባለ ክርስቶስን ያለመጠራጠር የሚከተሉ፣ አድርጉ ያለውን የሚያደርጉ፣ አታድርጉ ያለውን የማያደርጉ ሁሉ የጌታ አካል ናቸው። ማለትም ክርስቲያን (የክርስቶስ ተከታዮች) ናቸው። (ትዕዛዙን ሳይጠብቁ ክርስቲያን ነኝ ማለት አይሰራም!) ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ደግሞ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካላት ናቸው። "እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ።"(1ኛቆሮ 12:27) ከላይ በተረጎምነው መሰረት ደግሞ ቤተክርስቲያን ማለት የጌታ አካል ማለት ነው። ታዲያ በአማን ትዕዛዙን ከጠበቁ፣ ሕጉን ካከበሩ ከቅዱሳን በላይ ቤተክርስቲያን ለመሆን የተገባ ማን አለ? ከሁላችን በላይ እነርሱ የጌታ አካላቱ ናቸውና። ቤተክርስቲያን በቅዱሳን ስም መሰየም የለበትም የሚሉ ሰዎች ይህን የክርስቲያኖችን ቤተክርስቲያንነት በቅጡ የተረዱት አይመስለኝም።

ከዚህ በተጨማሪ ቤተክርስቲያናችን አጥቢያዎቿን በቅዱሳኑ ስም ለመሰየም ያመላከታት በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ የሚገኘው ኃይለ ቃል ነው። "እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ፣ ደስ የሚያሰኝኝንም ነገር ስለሚመርጡ፣ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና። በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ።" ኢሳ 56÷4-5 በዚህም ኃይለ ቃል ውስጥ ትዕዛዛቱን የመጠበቅ ነገር በአጽንዖት ሲጠቀስ ይታያል። "እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ፣ ደስ የሚያሰኝኝንም ነገር ስለሚመርጡ፣ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች..." ሲል ያንን ያመላክታል። ግን ጃንደረባ ሲባል ምንድነው? የሚለውም መታየት አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ አገባብ ጃንደረባ የሚለው ቃል ብዙ ትርጉሞች አሉት። ሁሉንም ግን የሚከተለው የጌታችን ቃል ይጠቀልላቸዋል። " በእናት ማህጸን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው።" (ማቴ 19:12) ስለዚህ ጃንደረባ ማለቱ ስለእግዚአብሔር መንግስት ብለው ራሳቸውን ስለሰለቡ (ከፍትወት ስለራቁ) ቅዱሳን ካልሆነ በቀር ስለየትኛው ዓይነት ጃንደረባ ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር መንፈስ ነውና የሚገደው መንፈሳዊው ሥራ እንጂ ነው። በእናት ማኅጸን ጃንደረባ ሆኖ ከመወለድም ሆነ በሰው ከመሰለብ ውስጥ ምን መንፈሳዊነት አለ? መጽሐፍ ቅዱስን እንዲህ እርስ በእርሱ እያተራጎሙ በምልዓት መረዳት እስካልተቻለ ድረስ በአንድ ጥቅስ ላይ ተንጠልጥሎ መፍረዱ ረዥም ርቀት አያስሄድም።

ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢቱን ሲቀጥል በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ በማለቱ ቤተክርቲያናችን አጥቢያዎቿን ብቻ ሳይሆን በአጸዷ ያሉትን ነገሮች ሁሉ (ጸበሉን ለምሳሌ) በቅዱሳን ስም ትሰይማለች። አንዳንዶች ስህተታቸውን ላለማመን መጨረሻ የሚመዙት "ይህ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ነው፤ ለሐዲስ ኪዳን አይሰራም።" ዓይነት የስንፍና ሐሳብ እንዲከሽፍም ወረድ ብሎ የማይጠፋ የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ ማለቱ መልስ ነው። ለዘለዓለም ያለን ትርጉም እስካልተቀየረ ድረስ።

፫. ዝክረ ቅዱሳን

አቡነ ዓቢየ እግዚእ

አቡነ ዓቢየ እግዚእ የተወለዱት በአስራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትግራይ ተንቤን (መረታ) ውስጥ ነው። የተባረኩ ወላጆቻቸው ያፍቅረነ እግዚእ እና ጽርሐ ቅድሳት ይባላሉ። አጥምቀው "ዓቢየ እግዚእ" ሲሉ ስም ያወጡላቸው የወቅቱ ጳጳስ ሰላማ መተርጉመ መጽሐፍት ናቸው። **ትርጉሙም "በጌታ ዘንድ ታላቅ ሰው" ማለት ነው።**

ዓቢየ እግዚእ በህጻንነታቸው ለሊት ለሊት ባሕር ውስጥ ሰጥመው ሲጸልዩ አድረው ቀን ቀን አባ ዘርዓሚካኤል ከተባሉ አባት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችንም መንፈሳዊ ትምህርቶችን በመማር ብሉይ ከሐዲስ ጠነቀቁ። ገና በወጣትነታቸው ወደ ታላቁ መነኩሴ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ደብረ በንኮል ሔደው መንኩሰዋል።

በገዳሙ በጾም፣በጸሎት እና በስግደት ተወስነው ከኖሩ በኃላ ከዚህ አገፋት ከሚባል ቦታ ወደ ደብረ ዓባይ ገዳም በዝሆን ተጭነው ሄደዋል። እዛም ከቅዱሳን በረከት ተቀብለው እንደገና ወደ ዋልድባ ሔደው የተሰወረች ቤተክርስቲያን አግኝተዋል። በጊዜው ለአርባ ቀን ብቻ አንዲት ቅጠል ብቻ ለቁመተ ሥጋ ይበሉ ነበር።ከዚያም ወደ ሀገራቸው ተንቤን ተመልሰው ዛሬም ድረስ ድንቅ ሆኖ የሚታየውን ገዳም መስርተው ብዙ መናንያን አፍርተዋል። ዓቢየ እግዚእ ገዳማዊ እና ጻድቅ ብቻ ሳይሆኑ ሐዋርያዊ አባትም ነበሩ። ከትግራይ እስከ ደንቢያ ደግሞ ሀገረ ስብከታቸው ነው። አንድ ጊዜ ደቀ መዛሙርትን አስከትለው ለስብከት ሲንቀሳቀሱ ተከዜ ወንዝ አካባቢ ደረሱ ቀኑ ነሐሴ አስር ነውና ተከዜ እስከ ገደፉ ሞልቶ ለሶስት ቀናት ባለመጉደሉ ከአንድ ሺ በላይ ሰዎች ሲያለቅሱ ደረሱ። ጻድቁ በአካባቢው የነበሩት ኢአማናውያን (አህዛብ) ቢሆኑም ራርተዋልና "አምላከ ሙሴ" ብለው ጸልየው ወደ ጥልቁ ውስጥ ገቡ። ቅዱስ ሚካኤል አብሯቸው ነበርና ተከዜ ግራና ቀኝ ተከፍሎ መሀሉ የብስ ሆነ። ይህን ድንቅ ያዩ ከዘጠኝ መቶ አርባ አንድ በላይ አህዛብ አምነው በጻድቁ እጅ ተጠምቀዋል። ይህም ዘወትር ነሐሴ አስር ቀን በቤተ ክርስቲያናቸው (ጎንደር) ይከበራል። ከዚያም እያስተማሩ ጎንደር ደረሱ። ያኔ ጎንደር በቀሃና አንገረብ ወንዞች የታጠረች አንዲት መንደር ነበረች። ጻድቁ ቀን ቀን እየሰበኩ ማታ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናቸው የታነጸበት ሥፍራ ላይ ሲጸልዩ ያድሩ ነበር። በዚያን ዘመን ጎንደር ውስጥ ጅብ፣እባብ እና መሠል አራዊት



ገብተው ህዝቡን ጨረሱት። ይህንን የተመለከቱት አቡነ ዓቢየ እግዚእ ወደ እግዚአብሔር አለቀሱ።በፍፁም ልባቸውም ስለ ህዝቡ ለመኑ።የለመኑትን የማይነሳ ጌታ ወደ ጻድቁ ቀርቦ "በስምህ የተማፀኑ፣በቃል ኪዳንህ ያመኑ፣በምድር አራዊት አይሰለጥኑባቸውም ፣በሰማይም እሳትን አያዩም፣ጎንደርም አራዊት ገብተው ሰውን አይጎዱም።"ብሏቸውል ጻድቁም የወንጌል አገልግሎታቸውን ፈፅመው ወደ ገዳማቸው ተንቤን ተመልሰዋል።

ጻድቁ አቡነ ዓቢየ እግዚእ ወደ ኢየሩሳሌም በደመና ሰረገላ ተጭነው፣ በመሄድ የጌታን መቃብርና ጎልጎታን በመሳለም ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን ከአቡነ እንጦንስና ከአቡነ መቃርስ መቃብር አፈራቸውን ለበረከት ይዘው በመምጣት በገዳሙ በትነውታል።

ንዕማን ከቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ሁለት የበቅሎ ጭነት አፈር ወደ አገሩ እንደወሰደ፣ እንዲሁም ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ከተቀበሩበት መቃብር ከሮም፣ ከደብረ ምጥማቅ ከእመቤታችን ገዳም፣ ከሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ መቃብር፣ ከአክሱም ጽዮንና ከሌሎችም ቅዱሳን መካናት፣ አፈራቸውን ያዙ።

መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል "ገዳምህ ይዘኸው ብትሄድ ለሰውና ለእንስሳት መድኃኒት ይሆንልሃል። ገዳምህ ልዩ ስሙ ተንስሐ በተባለ ቦታ ነው" ብሎ በራእይ ስለነገራቸው ህዳር 20 ቀን በብርሃን ሰረገላ ተጭነው የተቀደሰውን አፈር በትነውታል።

ጻድቁ አቡነ ዓቢየ እግዚእ ልዩ ልዩ ተአምራት በእግዚአብሔር ኃይል አድርገዋል። ለምሳሌ ያህል

1. የጻድቁ አባታችንን የተቀደሰውን አፈር ይዘው ሲመጡ መምጣታቸውን ያወቁ ተንስሐ በሚባል ገዳም የተቀበሩ ቅዱሳን አባቶች፣ ልክ እንደ አልዓዛር ከመቃብራቸው በመነሳት ጻድቁ አባታችንን ተቀብለዋቸዋል። ጻድቁ አባታችን ዓቢየ እግዚእም በብርሃን ሰረገላ ወርደው ባርከዋቸዋል።
2. አጼ ገብረመስቀልና የመንፈስ ቅዱስ ጓደኛቸው አቡነ ብእሴ እግዚእ የተባሉት አብረው እያሉ ሁለት ሰዎች ሞተው ወደ ቀብር ሲወስዷቸው በስውር በእግዚአብሔር ስም ጸልየው ከሞት አስነስተዋቸዋል። ይህ ተአምር የተደረገው በአክሱም ጽዮን ውስጥ ነው። ይህንን የአቡነ ዓቢየ እግዚእ ቅድስና የገለጹት አቡነ ብእሴ እግዚእ ናቸው።
3. በተጨማሪም ኤልያስ በመጎናጸፊያው ዮርዳኖስን ወንዝ መትቶ ከኤልሳዕ ጋር በደረቅ እንደተሻገሩ እና ሙሴ የኤርትራን ባህር ከፍሎ እስራኤላውያንን እንዳሳለፋቸው ሁሉ ጻድቁ በነበሩበት ወቅት የተከዜን ወንዝ ሞልቶ ብዙ ነጋድያንና አረማውያን ተጨንቀው እያሉ የተከዜን ወንዝ በመባረክ ውሃዉን አቁመው እንዲሻገሩ አድርገዋል።(ነገ ካልዕ 1:7-10፣ ዘዳ 14:10-30)

ይህንን ድንቅ ተአምር የተመለከቱ ከ 900 በላይ የሚሆኑ እስላሞች: የእግዚአብሔርን ቸርነትና የጻድቁን ድንቅ ሥራ በማድነቅ ወደ አባታችን ዓቢየ እግዚእ በመቅረብ ተጠምቀው ወደ ክርስትና እምነት ተመልሰዋል።ጻድቁ አባታችን አቡነ ዓቢየ እግዚእ ኢልክን በተባለ ከመቀሌ 10 ኪሜ ርቀት ላይ በሚገኝ ቦታ ሱባኤ ይዘው ይጸልዩ ነበር። በዚህ ስፍራም በስማቸው በፈለቀው ጠበል ብዙ የካንሰር (የነቀርሳ) በሽታ ታማሚዎች እየዳኑ ናቸው።ጻድቁ አባታችን አቡነ ዓብየ እግዚእ ከማረፋቸው በፊት አጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ የተገለጹበት ቦታ ከምርፋቁ በላይ ባለው ተራራ ላይ ይገኛል።

ቅድስት ሥላሴ የገቡላቸው ቃል ኪዳንም -- በስምህ የዘከረ፣ የመጸወተ፣ ገድልህን የሰማ፣ ቤተ ክርስቲያንህን ያሳነጸ፣ በዚህ ቦታ መጥቶ የጸለየውንና የቆረበውን እስከ 30 ትውልድ እምርልሃለሁ ብሏቸዋል። የተሰቀልኩባት፣ የተቀበርኩባት የቀራንዮ፣ የእናቴ የማርያም እንዲሁም የቅዱሳኑን መቃብር አፈር በዚህ ቦታ ስለበተንከው ቦታው እንደ ኢየሩሳሌም ይሁንልህ ብሎአቸዋል።

ጻድቁ አቡነ ዓብየ እግዚእ በጾምና በጸሎት፣ በትምህርት እንዲሁም የክርስቶስን ወንጌል በማስፋፋት፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽ ሃይማኖታዊ ገድላቸውንና ሩጫቸውን ከፈጸሙ በኋላ በ190 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም ወደ ማያልፈው ዓለም መንግሥተ ሰማያት ተሸጋግረዋል።

የጻድቁ መቃብር ያለው በቤተ ክርስቲያኑ መቅደስ ውስጥ ነው። ግንቦት 19 ቀን በገዳሙና በስማቸው በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በታላቅ መንፈሳዊ አከባበር ይከበራል።

የጻድቁ በረከት ጸሎትና ረድኤት ካንዣበበው መከራ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅልን አሜን !!

፬. ሰሞነኛ

ደብረ ታቦር



በዓለ ደብረ ታቦር የሚውለው በነሐሴ 13 ቀን በመሆኑ ለጸሙ ፍልሰታ ሱባዔ ልዩ ምዕራፍ ሆኖ በታላቅ መንፈሳዊ ተመስጦና ማኅሌት ይከበራል። **ከዘጠኙ ዐበይት የጌታችን በዓላት አንዱ ነው**። ምን አድርጎበታል ቢሉ ብርሃነ መለኮቱን ለሐዋርያት በደብረ ታቦር ገልጸበታል። ደብር ተራራ ታቦር የተራራ ስም ነው። ጌታ በመዋዕለ ስብከቱ ብዙውን ጊዜ የሚያስተምረው ተአምራት የሚያደርገው በተራራ ላይ ነበር። በዚህም ዕለት ዘጠኙን ከእግሩ ደብር ትቶ ሶስቱ ጴጥሮስን ዮሐንሰንና ያዕቆብን አስከትሎ ከርእሰ ደብር ወጣ። ወተወለጠ ራዕዩ በቅድሜሆሙ ወአብርሀ ገጹ ከመ ፀሐይ ወአልባሲሁኒ ኮነ ጸዓዳ ከመ በረድ ይላል መልኩ ተለውጦ ፊቱ እንደ ጸሐይ አብርቶ ልብሱ እንደ በረድ ነጭቶ ሙሴና ኤልያስ በቀኝ ሆነው ታዩአቸው። **ሙሴንና ኤልያስን መምረጡ ስለምንድነው ቢሉ** ሙሴ 570 ጊዜ ቃል በቃል ተነጋግሮ ባይህ እወዳለሁ አለው ፊቴን አይቶ አንድ ሰዓት እንኳ መቆም መቆየት የሚቻለው የለም አለው ። ይህማ ካልሆነማ ባለሟል መባሌ ምኑ ላይ ነው። ቢለው ኃላ ሰው ሆኜ ስመጣ እታይሃለው ብሎት ነበርና ዘጸ 33:18-23 ነው። ያን ለመፈጸም ኤልያስም እንዲሁ ተስፋ ነበረውና አንድም ጌታ ዕውር ቢያበራ ሙት ቢያነሳ ሙሴ ነው ኤልያስ ነው ብለውት ነበርና የኛን ጌታ ማን ሙሴ ማን ኤልያስ ይልሀል የሙሴ የኤልያስ ጌታ ይበሉህ እንጂ ብለው እንዲመሰክሩ አምጥቷቸዋል። ፍጻሜው ግን ደብረ ታቦር የመንሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት። ሕጋውያንም ደናግልም እንዲወርሷት ለማጠየቅ ከሕጋውያን ሙሴን ከደናግል ኤልያስን አመጣ።

ጴጥሮስ እመሰ ትፈቅድ ንንበር ዝየ ወንግበር ሠለስተ ማኅደረ አሐደ ለከ አሐደ ለሙሴ ወአሐደ ለኤልያስ ብትወድስ አንዱን ላንተ አንዱን ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ ሶስት ጎጆ ሠርተን በዚህ እንኑር አለው። መጽአ ደመና ብሩህ ወጸለሎሙ ይላል ። ይህን ሲናገር ብሩህ ደመና መጥቶ ጋረዳቸው ወዲያውም ዝንቱ ውእቱ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ ቢሉ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው። እሱን ስሙት የሚል ድምፅ ከወደ ላይ ተሰምቷል ።እነ ጴጥሮስ ደንግጠው ወደቁ ተንሥኡ ወኢትፍርሁ ብሎ አንስቷቸዋል ። ከርእሰ ደብር ሲወርዱም ያዩትን የሰሙትን እስከ ትንሳኤው ለማንም እንዳይናገሩ አዟቸዋል ።ማቴ 17 :3-9 **ዘጠኙን በእግረ ደብር ትቶ ሶስቱን አስከትሎ መውጣቱ ስለምንድነው ቢሉ** ከዘጠኙ ብርሃነ መለኮት ሊያይ የማይገባው ይሁዳ ነበርና ትቶትም ቢሄድ ለየኝ ባለ ነበርና አንድም ጴጥሮስ እሞታለሁ እነሣለሁ ቢለው ካንተ ይራቅ ብሎት ነበርና እሱን ስሙት የሚለውን እንዲሰማ አምጥቶታል። ዮሐንስና ያዕቆብንም በመንግሥቱ በመጣ ጊዜ በቀኝ በግራ መቀመጥን ሽተው ነበርና ነው። ያስ ቢሆን **ከተራሮች ሁሉ ታቦርን ስለምን መረጠ ቢሉ** ዳዊት ታቦር ወአርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌስሑ መዝ 87:12ብሎ ያን ለመፈጸም ነው።

፭. ነገረ ሃይማኖት

‹‹ እመ እግዚአብሔር - የእግዚአብሔር እናት››

ሰላመ እግዚአብሔር ይብዛላችሁ እንደምን ሰነበታችሁ እግዚአብሔር በረዳን መሰረት በዚህ ወር የምንመለከተው የምንነጋገረው ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሲሆን እርሱም ቅድስት ፣ ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እመቤታችን ከምታስተምረው አስተምህሮ መካከል ስለ እግዚአብሔር እናትነቷ የምንመለከት ይሆናል አምላከ ቅዱሳን አማኑኤል ጥበብና ማስተዋሉን ያድለን።

እግዚአብሔር አምላካችን ለአዳም አባታችን ያድነው ዝንድ የገባለት የቃልኪዳን ዘመን በደረሰ ጊዜ ከመላእክቶች መካከል ታላቁን መልአክ ቅዱስ ገብርኤልን ወደ አንዲት ድንግል ይልከው ዘንድ ወደደ ‹‹**ተውቦ ምህረት ለሚካኤል ፣ ወብስራት ለገብርኤል ፣ ወሃብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል - ምህረትን ለሚካኤል ፣ ብስራትን ለገብርኤል ፣ ሰማያዊ ሃብትን ለድንግል ማርያም ሰጠ››** እያለ በሥርዓተ ቅዳሴ ላይ እንደሚያነሳው ለብስራት የተመረጠው ቅዱስ ገብርኤል ድንግልን ያበስራት ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ። እግዚአብሔር በኦሪቱ ጊዜ በነቢያቱ እያደረ ብዙ ትንቢት የተናገረላት ማለትም አባቷ ዳዊት ‹‹**ልጀ ሆይ ስሚ አድምጪም የአባትሽንና የእናትሽን ቤት እርሺ ንጉስ ውበትሽን ወዷልና እሱ አምላክሽ ነውና››** እንዳለ በሦስት ዓመቷ ቅዱስ አባቷ ኢያቄምና ቅድስት እናቷ ሃና ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው ሰጧት አምላካችን እግዚአብሔርም ቅዱስ ፋኑኤልን ህብስተ ሰማያዊና ስቴ ሰማያዊ ይመግባት ዘንድ ለተልእኮ አሰማራው ። ስለዚህም ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ሃርን ከወርቅ አስማምታ እየፈተለች ቅዱሳት መጻህፍትን እያነበበች እየተማረች በቤተ መቅደስ አስራ ሁለት ዘመናትን ተቀመጠች።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ አስራ ሁለት ዘመን ከኖረች በኋላ የአዳም ጥንተ ጠላት ዲያቢሎስ ጦሩን ሰብቆ ተነሳ ይህ ማለት ድንግል ማርያም የአስራ አምስት አመት ብላቴና የነበረችበት ወቅት ማለት ነው። በዚህ ጊዜ ዲያቢሎስ አይሁዳዊያንን እና መጥቁል የተባለውን መሰሪ የሆነ ጠንቋይ በመጠቀም በድንግል ማርያም ተነሳባት መጥቁል ከሦስት መቶ ሳባ አጋንንት ጋር በመሆን ድንግልን ለማጥፋት ተነሱባት ድንግልም እግዚአብሔርን መከታ በማድረግ ድል አደረገች ይህን የተመለከቱ አይሁዳውያን ተነሱባትና ከመቅደስ እንድትወጣ ሆነ። አማናዊቷን መቅደስን ለመቅደስ ቀናይ የሆኑ በመምሰል ከመቅደስ መውጣቷን የተመለከተ እግዚአብሔር የአይሁዳዊያንን ክፋት የድንግልን ትህትና ተመልክቶ ወደዳት ቅድስት ሥላሴም ስለወደዷት እናቱ ትሆን ዘንድ አጫት።

ድንግል ማርያም በቤተ ዮሴፍ በገባች ጊዜ የሙት ልጅ የሆኑትን የዮሴፍን ልጆች አይታ እናታዊ እንክብካቤ ለማድረግና ከቆሻሻቸው ለማጽዳት ንጹሃን ለማድረግ ስትል ውሃ ለመቅዳት ማድጓዋን አንስታ ወደ ያዕቆብ ጉድጓድ አቀናች፡ ፡ በዚያም ውሃን ቀድታ ስትወጣ የተጠማ ውሻ በማግኘቷም በወርቅ ጫማዋ ስታተጣው ርህራሄዋ ከሰው አልፎ ለእንስሳት ጭምር

መሆኑን ስትገልጥ አይሁዳውያን ሴቶች ዘበቱባት በዚህ ጊዜ ነበር ከበጎ ስራ በኋላ ቅዱስ ገብርኤል መጣና ያበሰራት ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ እያለ ሲያበስራት ድንግል ማርያምም እንደምን ያለ ሰላምታ ነው አለችው። ቅዱስ ገብርኤልም ንግስቲቱ የነገረችውን ትዕዛዝ ተቀብሎ ዞር አለ ትቶ መሄድን ግን አልወደደም ሙሽራው ባህርየ መለኮት ወደ ሙሽሪት ባህርዬ አዳም ለሽምግልና ልኮታልና ምክንያት ፈልጎ የሙሽራውን ማንነት አስረድቶ ገልጾ እሽ ያስብላት ዘንድ ወዷልና ተመልሶ በቤተ ዮሴፍ ሳለች ብስራቱን ዜናውን ይነግራት ዘንድ ድጋሚ መጣ። ድንግል ማርያምም ይህ ነገር ደጋገመኝ በማለት ወደ ቤተ መቅደስ ሄጄ ልሰማው ይገባል ከእግዚአብሔር ከሆነ በቤተ እግዚአብሔር ይገለጣልና በማለት ወደ ቤተ መቅደስ ገባች።

የአስራ አምስት አመቷ ለዮሴፍ የታጨችው ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ሃርና ወርቅ አስማምታ ስትፈትል ከእግዚአብሔር የተላከው ቅዱስ ገብርኤል በመግባት ከዘመዶቿ ወገን የምትሆን ከካህናት መካከል አንድ ካህን ነበር ሰሙ ዘካርያስ የሚባል ተብሎ ወንጌል ለመሰከረለት ካህን የተዳረች ኤልሳቤጥ በሽምግልናዋ ዘመን እግዚአብሔር ጎብኝቷት ሴቶች ከወለዱት መካከል ታላቅ የሆነውን ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮትን ከጸነሰች ስድስት ወር ሆናት በማለት መጽነሷን ነገራት ድንግልም ኤልሳቤጥ በወንድ ዘር ጸነሰች እኔ ግን ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆንልኛል በማለት መለሰች። ቅዱስ ገብርኤል ለእግዚአብሔር የሚሰነው ነገር የለም ባላት ጊዜ ለእርሱማ የሚሳነው የለም በማለት እንዳልከኝ ይሁንልኝ በማለት ፈቀደች በዚህ ጊዜ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ ድንግል በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ወለደች። ልጇ በመጀመሪያ ቃል የነበረ እግዚአብሔር ቃል ሁሉ በእርሱ የሆነው ያለእርሱ ምንም የሆነ የሌለ ፍቃዷን በሰጠች ጊዜ ከስጋዋ ስጋን ከነፍሷ ነፍስን በመንሳት ፍጹም ሰው ሆነ። ዮሐ 1፡1-14 ይህንም በማድረግ እርሱ አምላክ ወሰብዕ ሆኖ እሳንም ድንግል ወእም እንድትሆን ፈቀደላት። የእግዚአብሔር እናትነቷ ድንግልናዋን አልሻረውም።

፮. ብሂለ አበው

በእንተ ጾም

የጾምን በጎነት ሥጋን ከመብላት በመከልከል ብቻ እንዳትወስነው ተጠንቀቅ። እውነተኛ ጾም ከክፉ መለየት ነው። [ስትጾም የታሠርክበትን] የክፉ ሥራ [የኃጢአት] ገመድ ፍታ፤ ክፉ ያደረገብህን ባልንጀራህን ይቅር በለው የበደለህን ሁሉ ተውለት። ለጠብና ለክርክር አትጹም።

ቅዱስ ባስልዮስ

በመጾም እየደከምን ሳለ የጾም አክሊልን ካላገኘን ፥ እንዴትና በምን ዓይነት አኳኋን ይህን ልንፈጽመው እንደሚገባው ልንረዳ ያስፈልጋል። ፈሪሳዊዉም ጾሞ ነበርና ፤ ከዚያ በኋላ ግን ወደ ቤቱ የኼደው ባዶ እጁንና የጾሙን ፍሬ ሳያገኝ ነውና (ሉቃ.18፡12)። ቀራጩ ደግሞ በአንጻሩ አልጾመም ነበር፤ ነገር ግን ከጾመው ፈሪሳዊ ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው እርሱ ነው። ይህም የኾነበት ምክንያት [ቀራጩ ባይጾምም ተጠቀመ ፤ በመፃዒ ሕይወቱም ጾም አላሻውም ለማለት ሳይኾን ከተአምኖ ታጣውእ ጋር] ሌሎች ግብራት ካልተከተሏት በቀር ጾም ረብ ጥቅም እንደሌላት [እና ትሕትና የጾም አጣማጅ መኾኑን/ የምትሠምረው ከትሕትና ጋር መኾኑን] እንድታውቅ ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ጾምን እንፁም ወንድሞቻችንን እንዉደድ። የጾምን ታላቅነት ተመልከቱ ጾም ለሰነፎች ሀዘን ስትሆን ለአዋቂዎች ደስታ ናት፤ ጾም የነፍስን ቁስል ታድናለች።የስጋ ፍላጎቶችንም ፀጥ ታደርጋለች። ለወጣቶች{ጎልማሶች] ፀጥታን መረጋጋትን ታስተምራቸዋለች።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ

ጾም መናኝ ነፍስ ስለሆነ በምናኔ ውስጥ ያለ ባልንጀራ ሥጋውን ይዞ ይጓዛል እንጂ ብቻውን አይጓዝም። ጾም ማለት የተራበ ሥጋ ማለት አይደለም የመነነ ሥጋ እንጂ። ጾም የሥጋ ረሀብ አይደለም የሥጋ ልዕልና እና ንጽህና እንጂ ለመብላት የሚናፍቅ የሚራብ ሰውነት ያለበት ሁኔታ ማለትም አይደለም፤ መብላት ዋጋውን የሚያጣበትና ሰውነት ለመብላት ካለው ፍላጎት ራሱን የሚያላቅቅበት ሁኔታ እንጂ።

አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ

ሐኪሞች በአንድ ታማሚ ሰውነት ውስጥ ያለውን ቆሻሻ፣ መርዘኛ ፈሳሽን ማስገድ ሲፈልጉ መጀመሪያ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ታማሚው ምግብ ከመውሰድ እንዲቈጠብ ነው። ታማሚው ለጊዜው ምግብን ከመብላት ካልተከለከለ ሐኪሞቹ የሚሰጡት መድኃኒት እንደተፈለገው ውጤት አይሰጥም። እኛም ቁስለ ነፍስ ቁስለ ሥጋ የምትፈውሰውን ጾም ስንቀበላት ከዚኽ በላይ ልንኾን ይገባናል ብዬ እነግራችኋለኹ። ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስን የምንሻ ከኾነ ልቡናችንን ንጹሕና ንቁ በማድረግ ልንወስዳት ይገባናል። እንዲኽ ካልኾነ ግን ከጥቅሟ ይልቅ ጉዳቷ ያመዝናል።

ቅዱስ_ዮሐንስ_አፈወርቅ

፲. ኪነ ጥበብ

ሌት እንኳ ሲበልጠው፤ ልቆ ከንጋቱ፤
እንዴት ነበር ያኔ ፤
ታቦር የቻለችው፤
ከርሱ አልፎ ተራራ
ፀአዳን ተኩላ እንዲያ ያማረችው።
እንዴት ነበር ያኔ!
በአምደ ብርሀን ውስጥ፤
የአብ ቃል ሲሰማ፤
የቆመ አካላችሁ አርፎ የተገኘው
በመውደቅ ሲቀማ።
ምን ነበር ስሜቱ
ትንቢቱ ሲፈፀም ፤
ሌት ብርሀን ሆኖ
ሲርቅበት መፅለም
እስኪ እንዴት ነበር ፤ የአምላክ ገቢሩ፤
''እረኞች''
ምሽት ቀን መስሏቸው ከሜዳ፤ ሲቀሩ፤
ወላድ ሙል ሙል ይዘው ፋለጋ የወጡት
ችቦን እያበሩ።
እንዴት ነበር ያኔ.....
ልክ.....ልክ
ታቦር እንደ ፈካች፤
ጨለማን ረስታ በብርሀን
እንደረካች ።

'' ደብረ ታቦር እና ኢትዮጵያ''
አንደ አምላክ መገለጥ በታቦር ተራራ
ፀሐይ ፍካት የለው፤
በደመና ሆኖ እንደ 'አብ'ስ ልሳን
መብረቅ ምን ድምፅ አለው።
ከፀሀይ ፀአዳ ፤
ከመብረቅ ማስገምገም፤
ከሚያስደነግጥ አፍ ፤
ከሀጫ በረድ መቅለም።
በእጥፉ ሲገለጥ፤ ከዚህ ሁሉ ሲያይል።
ብርሀን መልክ የለውም፤ ነጎድጓድም
አፍሮ በአፉ ምንም አይል፤
ማን እንደርሱ ይታያል
አጀብ አሰኝቶ፤
ተመልካቹን ሁሉ
መቆሙን አስቶ።
ግርምት ሚፈነቅል...
የተገለጠ አካል
ታየ ተራራ ላይ፤
ታቦር አርሞንየም
በሉ ተደሰቱ በስሙ አንድላይ።
''ጴጥሮስ ዮሐንስ ያዕቆብ''
በብርሀን ግባቱ ፤ሲታይ ሌላ ብርሀን
ምን ነበር ስሜቱ።
ከቀትሯ ፀሐይ

ልክ እንደዚ ሁሉ ሌቷ ብራ ሆኖ

ፀሊሟ ቢገፈፍ፤

ምነው ሀገሬም ላይ

ሰላም ብርሀን ወጥቶ የ

ከፋ ልብ ቢሰንፍ።

ምነው!

ልክ እንደዛች ታቦር

እርፍ ቢልላት በዙሪያዋ

ሁሉ የብርሀን አምዱ፤

የደደሩ ቂሞች

ላይታይ ከሰስሙው ደቀው ቢያምዱ።

ምነው

ደርሶ ብርሀን ቢሆን፤ የጨለማው ጊዚያት፤

ፀዳልን እስር አርጎ፤ ምሽቱ ቢለቃት።

እያልኩ አስባለሁ በፈጠሪ ግባት

ታቦር እንደፈካ፤

ሀገረ ኢትዮጲያዬም

ዳፍንትቷ ተገለጦ በብርሀን ብትረካ።

፷. ወቅታዊ

ፍልሰታ ለማርያም

በነገረ ማርያም ተጽፎ እንደምናገኘው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጥር ፳፭ ቀን በ፶፱ ዓ.ም ከዚህ ዓለም ድካም በአረፈች ጊዜ ቅዱሳን ሐዋርያት ሊቀብሯት ወደ ጌቴሴማኒ ይዘዋት ሲሔዱ አይሁድ "እንደ ልጇ ተነሣች፤ ዐረገች እያሉ እንዳያውኩን በእሳት እናቃጥላት" ብለው በዓመጽ ተነሡ። ታውፋንያ የሚባል አይሁዳዊም አጎበሩን ይዞ ሊያወርዳት ሲል የእግዚአብሔር መልአክ ሁለት እጆቹን ቀጥቶታል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስን ጨምሮ እመቤታችንን በደመና ነጥቆ ወደ ገነት ወስዶ ከዕፀ ሕይወት ሥር አስቀመጣት።

ቅዱሳን ሐዋርያትም እመቤታችን ያለችበት ቦታ እንዲገለጥላቸው ባረፈች በስምንተኛው ወር ከነሐሴ ፭ ቀን ጀምረው ሱባዔ ገብተው እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ጀመሩ። ከዚህ ላይ "ስምንት ወር ሙሉ ምን ይዘው ቆይተው ነሐሴ ላይ ሱባዔ ገቡ?" የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። በእውነቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ከስብከተ ወንጌል፣ ከጸም፣ ከጸሎት፣ ከገቢረ ተአምራት፣ ተለይተው እንደማያውቁ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ምስክር ነው።



በመኾኑም እመቤታችን ካረፈችበት ቀን ከጥር ወር ጀምሮ እስከ ነሐሴ ድረስ ጥያቄያቸውንና ጸሎታቸውን ባያቋርጡም ከሰው ተለይተው ሱባዔ ገብተው ጾመ ጸሎት የጀመሩት ግን ከነሐሴ ፭ ቀን ጀምረው ነው። ቀድሞስ የክብር ባለቤት የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ኾነው እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ተሠውራባቸው እንዴት ዝም ብለው ይቀመጣሉ?

ሁለት ሱባዔ ካደረሱ በኋላም የነገሩትን የማይረሳ፣ የለመኑትን የማይነሳ እግዚአብሔር አምላካችን ጸሎታቸውን ሰምቶ ነሐሴ ፲፭ ቀን የእመቤታችንን ሥጋ ሰጥቷቸው በክብር ገንዘው በጌቴሴማኒ ቀብረዋታል። በሦስተኛው ቀንም እንደ ልጇ እንደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይታ ተነሥታለች። "ከመ ትንሣኤ ወልዳ፤ እንደ ልጇ ትንሣኤ" ያሰኘውም ይህ ታሪክ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ሲሰብክ ቆይቶ ደመና ጠቅሶ ከሀገረ ስብከቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ እመቤታችን ከሙታን ተለይታ ተነሥታ ወደ ሰማይ ስታርግ አገኛት። በዚህ ጊዜ "ቀድሞ የልጅሽን ትንሣኤ፤ ዛሬ ደግሞ ያንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁን?" ብሎ ትንሣኤዋን ባለማየቱ ሀዘን ስለ ተሰማው

ከደመናው ይወድቅ ዘንድ ወደደ። "ወፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ" እንዲል። እመቤታችንም "አይዘህ አትዘን፤ ባልንጀሮችህ ሐዋርያት ያላዩትን ትንሣኤዬን አንተ አይተሃል" ብላ ከሙታን ተለይታ መነሣቷንና እንዲነግራቸው አዝዛ የያዘቸውን ሰበን ሰጥታ ሰደደችው።

እርሱም ትዕዛዟን ተቀብሎ በክብር ከተሰናበታት በኋላ ወደ ሐዋርያት ሔዶ እንዳልሰማ እንዳላየ መስሎ "የእመቤታችን ነገር እንደምን ኾነ?" አላቸው። እነርሱም "አግኝተን ቀበርናት" ሲሉት "ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር እንዴት ይኾናል?" አላቸው። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ከዚህ በፊት የክርስቶስን ትንሣኤ መጠራጠሩን ጠቅሶ እየገሠጸ ስለ እመቤታችን መቀበር እነርሱ የሚነግሩትን ኹሉ መቀበል እንደሚገባው ለቅዱስ ቶማስ አስረዳው። ቅዱስ ቶማስም የያዘውን ያውቃልና ጸጥ ብሎ ሲሰማው ቆየ። ቅዱስ ቶማስም "አታምኑኝም ብዬ ነው እንጂ እመቤታችንስ ከሙታን ተለይታ ተነሥታ ስታርግ አግኝቻታለሁ" ብሎ የሰጠችውን ሰበን ለሐዋርያት ሰጥቷቸዋል፡ ፡ እነርሱም በእመቤታችን ትንሣኤና ዕርገት እየተደሰቱ ሰበኑን ለበረከት ተካፍለውታል። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚያስተምሩን በቅዳሴ ጊዜ ሠራዒ ዲያቆኑ በሚይዘው መስቀል ላይ የሚታሠረው መቀነት መሰል ልብስ፤ እንደዚሁም አባቶች ካህናት በመስቀላቸው ላይ የሚያደርጉት ቀጭን ልብስና በራሳቸው የሚጠመጥሙት ነጭ ሻሽ የእመቤታችን ሰበን ምሳሌ ነው።

በዓመቱ ቅዱሳን ሐዋርያት "ቶማስ የእመቤታችን ትንሣኤዋንና ዕርገቷን አይቶ እኛ እንዴት ሳናይ እንቀራለን?" ብለው ከየሀገረ ስብከታቸው ተሰባስበው ጌታችን ሥጋዋን እንዲሰጣቸው በጠየቁበት በዚሁ ወቅት ከነሐሴ ፭ ቀን ጀምረው ሱባዔ ቢይዙ ጌታችን ልመናቸውን ተቀብሎ ነሐሴ ፲፭ ቀን እመቤታችንን መንበር፤ ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን፤ እስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ እመቤታችንንም ሐዋርያትንም አቍርቧቸዋል፡ ፡ እነርሱም እመቤታችንን በዓይናቸው ከማየት ባሻገር አብረው ሥጋውን ደሙን ተቀብለዋል / ትርጓሜ ውዳሴ ማርያም/።

ይህንን ትምህርት መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ከነሐሴ ፩-፲፩ ያለው ሁለት ሱባዔ ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ ኾኖ በምእመናን ዘንድ መጾም እንደሚገባው ሥርዓት ሠርተውልናል /ፍት.ነገ. አን.፲፩/። ይህ ጾምም "ጾመ ማርያም (የማርያም ጾም)" ወይም "ጾመ ፍልሰታ ለማርያም (የማርያም የፍልሰቷ ጾም)" እየተባለ ይጠራል። ‹ፍልሰት› የሚለው ቃልም "ፈለሰ ሔደ፤ ተሰደደ" ካለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲኾን ትርጕሙም ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ አገር መሔድን ያመለክታል። ‹ፍልሰታ ለማርያም› ሲልም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ካረፈች በኋላ ከጌቴሴማኒ ወደ ገነት መወሰዷን የሚያስረዳ መልእክት አለው።

በጾመ ፍልሰታ በቤተ ክርስቲያናችን በየቀኑ በማኅሌቱ፣ በሰዓታቱና በቅዳሴው በሚደርሰው ቃለ እግዚአብሔር ነገረ ማርያም ማለትም የእመቤታችን ከመጸነሷ ጀምሮ እስከ ዕርገቷ ድረስ ያለው ታሪኳ፣ ለአምላክ ማደሪያነት መመረጧ፣ ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ፣ ክብሯ፣ ርኅርኄዋ፣ ደግነቷ፣ አማላጅነቷ፣ ሰውን ወዳድነቷ በስፋት ይነገራል። እመቤታችንን ከሚያወድሱ ድርሳናት መካከልም በተለይ ምሥጢረ ሥላሴን፣ ምሥጢረ ሥጋዌንና ነገረ ድኅነትን ከነገረ ማርያም ጋር በማዛመድ የሚያትተው ቅዳሴ ማርያም፤ እንደዚሁም ነገረ ድኅነትን ከምሥጢረ ሥጋዌ (ከነገረ ክርስቶስ) እና ከነገረ ማርያም ጋር

በማመሣጠር የሚያትተው ውዳሴ ማርያምም በስፋት ይጸለያል፤ ይቀደሳል፤ ይተረጐማል። በሰንበታት የሚዘመሩ መዝሙራት፤ በየዕለቱ በቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለተዋሕዶ በእግዚአብሔር መመረጧን፣ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን፣ ክብሯን፣ ቅድስናዋን፣ ንጽሕናዋን የሚያወሱ ናቸው።

በጾመ ፍልሰታ ባሕታውያን ብቻ ሳይኾኑ ዓለማውያንም በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በእመቤታችን አማላጅነት የሰይጣንን ፈተና ድል ለማድረግ እንዲቻላቸው ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው በየገዳማቱና በየአብያተ ክርስቲያናቱ በዓት አዘጋጅተው፣ ሱባዔ ገብተው፣ ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው አስገዝተው ይጾማሉ፤ ይጸልያሉ። እንደዚሁም ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ይቀበላሉ። እኛም የእመቤታችንን ዕረፍትና ትንሣኤ በማሰብ ከልጇ ከወዳጇ የሚገኘውን ጸጋና በረከት ተስፋ በማድረግ የአባቶቻችንንና የእናቶቻችንን ፈለግ ተከትለን በየዓመቱ ጾመ ፍልሰታን እንጾማለን፤ የምንችል ደግሞ አስቀድሰን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እንቀበላለን። በተጨማሪም ይህ ጾም ለእመቤታችን ያለንን ፍቅርም የምንገልጽበት ወቅት ነው። በተለይ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት በአብዛኛው ትምህርተ ወንጌል የሚማሩት፤ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን የሚቀበሉት በዚህ በጾመ ፍልሰታ ነው።

ኹላችንም ጌታችን በስሙ ሁለትም ሦስትም ኾነን ለጸሎትና ለመልካም ሥራ ብንሰባሰብ እርሱ በመካከላችን እንደሚገኝ የገባልንን ቃል ኪዳን መሠረት በማድረግ /ማቴ.፲፰፥፳/ በጾመ ፍልሰታ ሳምንታት በጌታችን፣ በእመቤታችንና በቅዱሳን ሐዋርያት ስም በቤተ ክርስቲያን ተሰባስበን ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመማር ባሻገር ብንጸም፣ ብንጸልይ፣ ብናስቀድስ፤ እንደዚሁም ሥጋውን ደሙን ብንቀበል በበረከት ላይ በረከትን፤ በጸጋ ላይ ጸጋን እናገኛለን። በኋላም ሰማያዊውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ እንችላለን።



ነገር ግን በሕግ የተከለከለ እስኪመስል ድረስ በዚህ ወቅትም ኾነ በሌላ ጊዜ ሥጋውን ደሙን የሚቀበሉ ወጣቶች ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህም አረጋውያንና ሕጻናት ብቻ ሳይኾኑ ወጣቶችም

ጭምር የመቊረብና የመዳን ክርስቲያናዊ መብት እንዳለን በመረዳት ራሳችንን ገዝተን፣ ንስሐ ገብተን፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ይገባናል። አምላካችን በማይታበል ቃሉ "ሥጋዬን የሚበላ፤ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው" በማለት ተናግሯልና /ዮሐ.፮፥፶፬/።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይኹን። የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ሐዋርያት ጸጋና በረከት አይለየን።

፱. ከሰሞኑ በረከት

ነሐሴ 7 ጽንሰታ ለማርያም

ከካም ወገን የምትሆን ቅድስት ሐና የምትባል ሚስት ያገባው ቅዱስ ኢያቄም የሚባል ከነገደ ይሁዳ የተወለደ አንድ ሰው ነበረ ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚወዱ እግዚአብሔር የሚወዳቸው ደጋጎች ነበሩ እግዚአብሔርም በሰራው ሕግ ጸንተው ይኖሩ ነበር። ሚስቱ ግን መክና ትኖር ነበር ። ልጅም ስላልነበራቸው አዝነው ተክዘው ይኖሩ ነበር ። ዕለት ዕለት ወደ ቤተ እግዚአብሔር እየሄዱ ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ በኀዘን በልቅሶ ልመናቸውን ወደ እግዚአብሔር ያቀርቡ ነበር ከገንዘባቸውም ከፍለው ለድሆች ለጦም አዳሪዎችና ለቤተ እግዚአብሔር ይሰጡ ነበር እግዚአብሔርም ልጅ በመስጠት ልመናቸውን ይቀበላቸው ዘንድ ይደረግልናል በማለት በተስፋ ጸንተው ይኖሩ ነበር።

ከዕለታት በአንድ ቀን ሐና ሚስቱና ኢያቄም ወጥተው ወደ ተክል ቦታ ገቡ። ቁመውም ሲጸልዩ ርግቦች ከልጆቻቸው ጋራ ደስ ባሏቸዉ ሲጫወቱ አይተው ልጅ ስለሌላቸው ፈጽመው አዘኑ ከኃዘናቸውም ብዛት የተነሳ አንቀላፍቷቸው ተኙ። ሐናም ተኝታ ሳለች በባሏ በኢያቄም እጅ በትር እንደተያዘች ያችም በትር አብባ አፍርታ አየች 2ኛም እሱ በሐና እጅ ከፍሬ ሁሉ የሚመስጠው የሌለ የሚጣፍጥ መልካም ፍሬ ተይዞ አየ። ከእንቅልፋቸውም በነቁ ጊዜ ደስ አላቸው በመኝታቸውም ስለ አዩት ነገር እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት ።

ከዚህም በኃላ ፈቃደ እግዚአብሔር ይሁን ብለው ወደ ቤታቸው ገቡ ከዚህም በኃላ ሐና ፀነሰች ፅንስዋም ታወቀ የሰጠኸኝን ልጅ ለእግዚአብሔር መባዕ አድርጌ እሰጠዋለሁም ብላ ለእግዚአብሔር ተሳለች ሁል ጊዜ በጾምና በጸሎት ተወስና በፍጹም ደስታ ለድሆችና ለጦም አዳሪዎች ምጽዋትን ስትሰጥ ኖረች ። ይህን ሁሉ ስላደረገልኝ ፈንታ ለእግዚአብሔር ምን ወሮታ አደርግለታለሁ ብላ በልቧ አሰበች ለመሥዋዕት የማይሆነውን ምግብ ሁሉ ከመብላት ትከለከል ነበር ስግደትንም ታበዛ ነበር የሰጣትንም ይጠብቅላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ልመናን አበዛች ። ከ6ኛው ወርም በኃላ የሐና ፅንሷ ታወቀ የእርሷ ዘመዶች የባሏም ዘመዶች በሰሙ ጊዜ ወደስዋ መጥተው የሕጻንነትሽ ዘመን ካለፈ በኃላ ላንቺ የተደረገ ይህ የምንሰማው ነገር ምንድን ነው አሏት መፀነሷንም ያዩ ዘንድ ማኅፀኗን ዳሰሱ። ዓይኗ የታወረ ከክብርት ሐና እናት ዘመዶች ወገን የአርሷን ልጅ የምትሆን እንዲት ሴት ነበረች ምን ምን ሳታውቅ ዓይኗን በዳሰሰች ጊዜ ፈጥና ዳነች ብፅዕት ሐናን ሐና ሆይ ምስጋና ይገባሻል አለቻት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እንደ አንቺ በማኅፀኑ የዕውራንን ዓይን የሚያበራ የለምና። ዘመዶቿም ሰገዱላት ብፅዕት ሐና ከአጥቢያ ኮከብ ጸሐይ እንዲከብር በእሳቸው ላይ ከበረች። ዝናዋም በየሀገሩ ሁሉ ተሰማ ድውያንን ሁሉ ሕሙማንንም ሁሉ እያመጡ ማኅፀኗን እየዳሰሱ ይፈውሱ ነበር ፍጥረትም ሁሉ በማኅፀንዋ ሳለ ሕሙም የፈወሰ በተወለደ ጊዜ እንደምን ያለ ይሆን አሉ።

የእስራኤልም ልጆች በሰሙ ገዜ ተሰብስበው ስለዚህ ነገር ምን እንላለን እነሆ ኢያቄምና ሐና የእስራኤልን መንግስት አጠፋ ሐና ፀንሳ ሳለች በማኅፀንዋ ታድናለችና በኛ ላይ ልትነግሥ አይደለምን አሉ። ከሳቸውም አንዱ ይህ ያስደንቃችኋልን ሙሴ እንደ ጻፈው በደንጊያ ወግረው እንገድላቸው ዘንድ

ኑ አላቸውና ሁሉም ተቃጠሩ መንፈቀ ለሊት በሆነ ጊዜ ስሙ ገብርኤል የሚባል መልአክ ከሰማይ ወርዶ በዘመድ የከበራችሁ ኢያቄም ሐና ሆይ ተነሡ አላቸው ሊባኖስ ወደሚባል ተራራም ወሰዳቸው እኛን ከአርዌ ሰይጣን ወጥመድ ታድነንና መፈራትን መወደድን የተመላች ስሟ ማርያም የምትባል በዚያ ተወለደች። ወደ ጥንት ነገራችን እንመለስና የፅንስዋም ወራት በተፈፀመ ጊዜ በግንቦት አንድ ቀን ከፀሐይ የምታበራ ሴት ልጅ ወለደች የመልኳም ደምግባት ከመዓር ከስኳር ይልቅ ደስ ያሰኛል የመዓዛዋም ሽታ ከሽቱ ሁሉ ይበልጣል ዘመዶቿና ጎረቤቶቿም በሰሙ ጊዜ ፈጽመው ደስ አላቸውና ተሰብስበው ወደእርሷ መጡ ወደእሷም መጥተው ልጅዋን ባዩ ጊዜ ፈጽመው አደነቁ እርስ በእርሳቸውም እንደዚህች ያለች ብላቴና ከቶ አይተን አናውቅም ተባባሉ ጸጋ እግዚአብሔርም ብርሃን በሰውነቷ ሁሉ መልቷልና ከኢያቄምና ከሚስቱ ከሐና ጋር ደስ እያላቸው የእግዚአብሔርን ቸርነት እየተናገሩ ሰባት ቀን ተቀመጡ ያችንም ብላቴና ስሟን ማርያም አሏት ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው።

ሰባቱምን ቀን በፈጸሙ ጊዜ በፍቅር ወደየቤታቸው ገቡ ኢያቄምና ሐናም ልጃቸውን ማርያምን ሲያሳድጉና ስለ ልጃቸው ለእርሳቸውም ስለ አደረገላቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ፈጽመው ሲያመሰግኑት ሦስት ዓመት ኖሩ በጾም በጸሎት ተወስነው ለድሆችና ለጦም አዳሪዎች ምጽዋት እየሰጡ በጎ ሥራ መሥራትን አበዙ ። ልጃቸውን ማርያምን በንጽሕና ሲያሳድጉ 3 ዓመት በተፈጸመ ጊዜ ሐና ባሏን ኢያቄምን ወንድሜ ሆይ ልጃችን ለቤተ እግዚአብሔር ብፅዓት አድርገን እንስጥ ልጃችን ቤተ እግዚአብሔርን ልታገለግል ነው እንጂ በዚህ ዓለም እኛን ልታገለግል እንዳልተሳልን አስብ አለችው ኢያቄም ይህን ነገር ከሚስቱ ከሐና በሰማ ጊዜ ፈጽሞ ደስ አለው ለመንገድ የሚሆን ስንቅና ለቤተ እግዚአብሔር የሚሆንም መባዕ ሁሉ አዘጋጀ ቤተሰቦቻቸውንና ባልንጀሮቻቸውን ዘመዶቻቸውንም ሁሉ ጠሩ ልጃቸውን ይዘው ሄደው ወደ ቤተ መቅደስ አስገቧት። ካህናት በቤተ መቅደስ ዩሉ ሁሉ በሰሙ ጊዜ እነሱን ለመቀበል ወጥተው መንፈሳዊ ሰላምታ ሰጧቸው ኢያቄምና ሚስቱን ሐናን ልጃቸውን ማርያምን አመሠገንዋቸው ። በአንብሮተ እድ ፈጽመው ባረኳቸው እግዚአብሔር ጎዘናችሁን በእውነት ተቀብሏችኃል ቸር በምትሆን በዚህች ልጅም ደስ አሰኝቷችኋል አሏቸው። እመቤታችንንም ለእግዚአብሔር እናትነት የተመረትሽ ክብርት ሆይ ፍቅር ይገባሻል አሏት ታቅፈው ይዘውም በታኅሣሥ ሦስት ቀን በእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ቤተ መቅደስ አስገቧት

ልመናዋ ክብሯም ለዘለዓለም በውነት በሁላችን ይደርብን ።